በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የመንግስት የልማት ድርጅቶች

ባለአደራ ቦርድ ላይ የክዋኔ ኦዲት

የክትትል ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2009

አዲስ አበባ

ማውጫ

ማውጫ i
ክፍል አንድ 1
መግቢያ 1
የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ አመሰራረት፣ 1
የባለአደራ ቦርዱ ዓላማ 1
የክትትል ኦዲቱ ዓላማ 2
የክትል ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 2
የክትትል ኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት 2
ክፍል ሁለት 3
በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣ 3
የባለአደራ ቦርድ የንብረት አወጋገድ መመሪያን በተመለከተ፣ 3
ባለአደራ ቦርድ እና የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፣ 5
የባለአደራ ቦርድ ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ንብረት እና ሰነድ ርክክብን በተመለከተ፣ 6
የባለአደራ ቦርድ የንብረት አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ፡- 7
የባለአደራ ቦርድ የንብረት አገማመት፣ የመነሻ ዋጋ አወሳሰን ፣ የጨረታ ሂደት እና የተሸጡ ንብረቶች አረካከብን በተመለከተ፣ 9
የባለአደራ ቦርድ የስራ እና ሰራተኞች መመሪያን በተመለከተ፣ 10
የባለአደራ ቦርድ የክፍያና የወጪ አጠቃቀም መመሪያን በተመለከተ፣ 11
ባለአደራ ቦርዱ በተለያየ መንገድ ይዞታቸው ከተለወጡ እና በኪሳራ ምክንያት ከፈረሱ የልማት ድርጅቶች የተረከባቸውን የማይተላለፉ ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ መሰብሰባቸውን፣ ተከፋይ ሂሳቦች በአግባቡ ተጣርተው የሚከፈል መሆኑን የሚያረጋግጥ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤ 12
የፈረሱ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ለማጣራት የተዘጋጀ እቅድ እና የእቅድ ክንውኑን በተመለከተ፣ 13
ክፍል ሦስት 15
መደምደሚያ 15
ክፍል አራት 18
የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation) 18

ክፍል አንድ

መግቢያ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ አመሰራረት፣

1. በአገራችን የነበረውን የእዝ ኢኮኖሚ ስርዓት ወደ ነፃ ኢኮኖሚ ስርዓት ለማሸጋገር በወጣው የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ይዞታ የማዛወር ሂደት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለቤትነት ሲቀየር በሶስተኛ ወገኖች ላይ የሚደርሰውን የመብት ጥያቄና ግዴታዎችን ተከታትሎ ለማስፈፀምና ሊከሰት በሚችለው የአፈፃፀም ክፍተት ላይ ጥንቃቄ ለማድረግ አንድ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ማቋቋም በማስፈለጉ የካቲት 5 ቀን 1988 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 17/88 "ወደ ግል ይዞታ የተዛወሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ" በሚል ስያሜ ተቋቋመ የፕራይቬታይዜሽን እንቅስቃሴው በሽያጭ ብቻ ሳይሆን የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የመዝጋት፣ ለቀድሞ ባለሃብቶች የመመለስ፣ በአክሲዮን ማህበርነት የማደራጀት ስራዎችን ሲጨምር ለቦርዱ ተጨማሪ ኃላፊነቶችን በመስጠት እንደገና በአዲስ መልክ "የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ በሚል ስያሜ ሰኔ 20 ቀን 1992 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 208/92 ተሻሽሎ ተቋቋመ፡፡
2. ባለአደራ ቦርዱ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን ተጠሪነቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ነው፡፡

የባለአደራ ቦርዱ ዓላማ

3. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ዓላማው የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታ በሚዛወሩበት፣ወደ አክሲዮን ማህበርነት በሚለወጡበት ወይንም ለቀድሞ ባለቤቱ በሚመለሱበት ጊዜ ወደ አዲሱ የግል ባለቤት፣ ወደ አክሲዮን ማህበሩ ወይንም ወደ ቀድሞ ባለቤቱ የማይተላለፉ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን መሰብሰብ፣ እዳዎችን መረከብና መክፈል፣ ንብረቶችን መረከብ፣ ማስወገድ እና ከነዚሁ ጋር የተያያዙ የፍርድ ቤት ጉዳዮችን መከታተልና ማስፈፀም እንዲሁም የሚፈርሱ የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ማጣራት ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

4. በባለአደራ ቦርዱ ውስጥ የሚከናወኑ ስራዎች ማለትም የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታ በሚዛወርበት፣ ወደ አክሲዮን ማህበርነት በሚለወጥበት ወይንም ለቀድሞ ባለቤቱ በሚመለስበት ጊዜ ወደ አዲሱ ባለቤት፣ወደ አክሲዮን ማህበሩ ወይንም ወደ ቀድሞ ባለቤቱ የማይተላለፉ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በአግባቡ በመሰብሰብ ወደ ልዩ ፈንዱ ገቢ መሆናቸውን፤ እዳዎችን መረከብ እና ለተፈቀደላቸው ተከፋይ ሂሳቦች ብቻ ወጭ አድርጎ መክፈሉን ፤የሚፈርሱ የልማት ድርጅቶችን በአግባቡና በወቅቱ ሂሳብ ማጣራቱን እንዲሁም የተረከባቸው ንብረቶች አያያዝ፣አጠባበቅ እና አወጋገድ በመንግስት መመሪያ መሰረት መሆኑን እንዲሁም የዋጋ ግመታው (valuation) ስርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ስኬታማና ብቃት ባለው መልኩ መከናወኑን ለማረጋገጥ መ/ቤታችን የክዋኔ ኦዲት አከናውኖ በገኛቸው ግኝቶች እና በተሰጡት ማሻሻያ ሃሰቦች ላይ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎችና የተዘረጉ የአሰራር ሥርዓቶች ለማረጋገጥ ነው፡፡

የክትል ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

5. ክትትል ኦዲቱ የሸፈነው በ2004 ዓ.ም የክዋኔ ኦዲት ሪፖርትና የኦዲቱ የሥራ ወረቀት (Working Paper) በሙሉ ክለሳ በማድረግ ሲሆን ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ነው፡፡ ክትትል ኦዲቱ የተከናወነው ባለአደራ ቦርዱ የኦዲት ግኝቱን ለማስተካከል ለመ/ቤታችን በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር ክለሳ በማደረግ ለሚመለከታቸው የባለአደራ ቦርድ የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ የአዲት ግኝቱን በተመለከተ በባለአደራ ቦርዱ የሚቀርቡ የሰነድ መረጃዎችን እና የኦዲት ማስረጃ በመሰብሰብ ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች እና የክዋኔ ኦዲትን በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት

6. የክትትል ኦዲቱን ለማከነወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

ክፍል ሁለት

በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣

የባለአደራ ቦርድ የስራ አመራር ቦርድ እና የዋና ዳይሬክተር ኃላፊነት በተመለከተ፣

7. ባለአደራ ቦርዱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን ውስጥ ያሉ ስራዎች (ከልዩ ፈንዱ የሚፈፀም ማንኛውም ክፍያ) በስራ አመራር ቦርዱ የሚያፀድቅ ሲሆን ከዚህ ውጭ ያሉ ስራዎች እንደ ጨረታ መነሻ ዋጋ መወሰን፣ የጨረታ ኮሚቴው በሚያቀርባቸው አማራጮች መሰረት ሽያጮች በሙሉ የማፅደቅ ስራዎች በማን እንደሚፀድቁ እና በምን መልኩ እንደሚከናወኑ በዋና ዳይሬክተርና በስራ አመራር ቦርድ በመለየት ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያልተዘጋጀ በመሆን የኦዲት ግኝቱ ነበር፡፡

8. በመሆኑም ባለአደራ ቦርዱ የመቋቋሚያ ዋጁን መሰረት በማድረግ በስራ አመራር ቦርድ እና በዋና ዳይሬክተር የሚሰሩ ስራዎችን በመለየት ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

9. ባለአደራ ቦርዱም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ የድርጊት መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

10. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ባለአደራ ቦርዱ ችግሮችን ለመቅረፍ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላከ መሆኑን፣

11. በክትትል ኦዲት ወቅት ለመ/ቤታችን በላኩት የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት በአለአደራ ቦርዱ ሁሉንም ውሳኔዎችን እንዲጸድቁ ለሥራ አመራራ ቦርዱ መላክ መቆሙንና ውሳኔዎችን በመንግሰት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የጨረታ መነሻ ዋጋን በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ማጸደቅ መጀመራቸውን፣ ሽያጮቹንም በሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ በማጸድቅ በመጨረሻም በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ እየተወሰነ ተግባራዊ ማድረግ መጀመራቸው ታውቋል፡፡

የባለአደራ ቦርድ የንብረት አወጋገድ መመሪያን በተመለከተ፣

12. ባለአደራ ቦርድ ከሚገለገልበት የንብረት አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 9/2003 በተሟላ ሁኔታ የማይተገብራቸው አንቀጾች በመኖራቸው፡-

13. ወደ ባለአደራ ቦርዱ የተላለፉ ቋሚ ንብረቶች ሥራ አመራር ቦርድ ሳይፈቅድና ዋጋቸው ሳይከለስ ከ1997 እስከ 2004 ዓ.ም እየተከራዩ መገኘታቸው፣ በናሙና ከታዩት 13 የተለያዩ መጋዘኖች፣ ሱቆችና ቢሮዎች ውስጥ 12ቱ (92%) በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሰረት ዋጋቸው ያልተከለሰ መሆኑን እንዲሁም የቡና ግዥና ሽያጪ ድርጅት ንብረት የሆነ አንድ ሞተር ሳይክል ቀደም ሲል በጨረታ የተሸጡ ሞተር ሳይክሎችን እንደመነሻ ዋጋ በመውሰድ ያለጨረታ የተሸጠ መሆኑ በኦዲት ግኝቱ ታይቶ ነበር፡፡

14. በመሆኑም ወደ ባለአደራ ቦርዱ የተላለፉ ቋሚ ንብረቶች አስፈላጊው መረጃ ተሟልቶላቸው ሊወገዱ እንደሚገባ እና ባለአደራ ቦርዱ እየተጠቀመበት ያለው የንብረት አወጋገድ መመሪያ የማያሰራው መሆኑን አሳውቆ ለስራው ተስማሚ የሆነ መመሪያ በሚመለከተው አካል አጸድቆ ስራ ላይ ማዋል እንደለበት በኦዲቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም ባለአደራ ቦርዱም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ የድርጊት መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

15. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ባለአደራ ቦርዱ ግኝቶቹን ለማስተካከል የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ በተላከው የድርግት መረሃ-ግብርም የተገለፀው በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት ከባለአደራ ቦርድ የሥራ በህሪ አንፃር የማያሰሩትን አንቀፆች በመለየት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር (አሁን የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር) ጥያቄ አቅርበው በደብዳቤ ቁጥር ገ/ኢ/ል/ሚ/1/11/66 በቀን 13/07/2004 እና በደብዳቤ ቁጥር ገ/ኢ/ል/ሚ/11/1/90 በቀን 26/10/2004 የተወሰኑት የተፈቀዱ በመሆናቸው ከ2005 በጀት ዓመት ጀምሮ ተግበራዊ ያደረጉ ሲሆን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አቅርበው ያልተፈቀደላቸው አንቀፆች በመመሪያ ቁጥር 9/20003 መሠረት እየሠሩ መሆናቸውን እና ባለአደራ ቦርድ የሚረከባቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ንብረት ተረክበው ማከራይት ዓላማ ባይሆንም እስኪወገድ ድረስ በኦዲት ግኝቱ በኋለ ያለጨረታ የሚከራይ ምንም ዓይነት ንብረት አለመኖሩ ባለአደራ ቦርድ ካከራያቸው ቢሮዎች፣ቤቶች እና መጋዝኖች የዋጋ ክለሳ የተደረገበትን፣ የኪራይ ውል

የተዋዋለበትን እና ለማከራየት የተዘጋጁ የጨረታ ሠነዶችን ክለሳ በማድረግ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ባለአደራ ቦርድ እና የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፣

16. ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ እና ባለአደራ ቦርድ በቅንጅት የሚሰሩበት የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ ባለአደራ ቦርዱ ያልተዘጋ ሂሳብ የሚረከብ መሆኑ (አደይ አበባ ድርና ማግ ፋብሪካ የ8 ዓመት ሂሳብ ሳይዘጋ)፣ ሰነዶች የሚጠፉ መሆኑ (በርክክብ ላይ የሚገኘው የቀድሞው ውሃ ጉድጓድ ስራዎች ድርጅት) በርክክብ ወቅት አለመገኘታቸው) እና በርክክቡ ወቅት ያልተገኙ ሰነዶችን በተመለከተ ተጠያቂ የተደረገ አካል የሌለ መሆኑን የኦዲት ግኝቱ ነበር፡፡

17. ባለአደራ ቦርዱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በተለይ ከፕራይቬታይዜሽንና ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ (ከአሁን የመንግሰት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር) ጋር (በሪፖርት አደራረግ፣ በእቅድ አዘገጃጀት ወዘተ) በቅንጅት የሚሰራበትን የጋራ መግባቢያ ሰነድ (መመሪያ) አዘጋጅቶ ሊጠቀም የሚገባ መሆኑን በኦዲት ሪፖርቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

18. በመሆኑም ባለአደራ ቦርዱም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

19. ባለአደራ ቦርዱ ከላይ የተጠቀሱትን ግኝቶች ለማስተካከል የድርጊት መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላኩ ሲሆን በድርጊት መርሃ-ግብሩ ላይ ባለአደራ ቦርዱ ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግሰት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ (ከአሁን የመንግሰት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር) ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያሰችል የመግባቢያ ሠነድ ጥናት ከህዳር 2005 ዓ.ም ጀምሮ የሚያከናወኑ መሆኑን ቢገልጹም በድርጊት መርሃ ግብሩ በተገለፀው መሰረት ባለአደራ ቦርዱ ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግሰት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ (ከአሁን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር) ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችላቸው ጥናት የክትትል ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ጥናትም ሆነ የተዘጋጀ የመግባቢያ ሠነድ የሌለ መሆኑን ታውቋል፡፡

የባለአደራ ቦርድ ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ንብረት እና ሰነድ ርክክብን በተመለከተ፣

20. ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ (አሁን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር) ለባለአደራ ቦርድ ንብረቶችን እንዲረከቡ ካሳወቃቸው ድርጅቶች በናሙና ተመርጠው ከታዩት ውስጥ አዲስ ጎማ ፋብሪካ፣ ደብረብርሃን ብርድ ልብስ ፋብሪካ እና የአዲስ የመለዋወጫ እቃዎች አስመጪና አከፋፋይ አክሲዮን ማህበር የእያንዳንዱ ንብረት ዓይነትና የዋጋ ዝርዝር አለመላኩ እና በአክሲዮን ማህበርነት ሲደራጅ በ (restructuring) ጥናቱ መሰረት ከካፒታል ውጭ የሆነ ብር 57,053,479 የሚያወጣ ንብረት በጥቅል ወደ ባለአደራ ቦርድ እንዲተላለፍ መደረጉ እንዲሁም ድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ 18 ሺህ ላይን አይተም እና ከብር 24 ሚሊዮን በላይ የሚገመት ንብረት ያለርክክብ ሠነድ ለቦርዱ የተላለፈ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጦ ነበር፡፡

21. ይህም በመሆኑ ባለአደራ ቦርዱ ንብረቶችን በሚረከብበት ጊዜ በመጠን፣በዓይነትና በዋጋ ተለይተውና ተዘርዝረው ሊረከብ የሚገባ መሆኑን በኦዲት ሪፖርቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

22. ባለአደራ ቦርዱም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

23. በክትትል ኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ባለአደራ ቦርዱ በኦዲት ግኝቱ ላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለማስተካከል የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለመ/ቤታችን ልኳል፡፡ በድርጊት መርሃ-ግብሩ ላይ የተገለፀው ባለአደራ ቦርዱ ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ (አሁን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር) የሚረከበውን ንብረቶች በመጠን፣ በዓይነትና በዋጋ ለይተው በዝርዝር የመረከቡ ሥራ ከህዳር 2005 ዓ.ም ጀምሮ የተረከባቸው ንብረቶች በዝርዝር፣ በመጠን፣ በዓይነትና በዋጋ ተለይተውና ተዘርዝረው መሆኑን ከ2005 ዓ.ም ወዲህ ባለአደራ ቦርዱ የተረከባቸው የልማት ድርጅቶች የርክክብ ቬርቫል ክለሳ በማድረግ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የባለአደራ ቦርድ የንብረት አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ፡-

24. ባለአደራ ቦርድ የተረከባቸውን ንብረቶች መቆጣጠሪያ መዛግብት የመያዝ፣ንብረቶችን የመረከብና ወጪ የማድረግ ሥራን አንድ ሰው እየሰራ የሚገኝ መሆኑ፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአክሲዮን ማህበርነት ሲደራጁ ከተፈቀደላቸው ካፒታል ውጪ የሆኑ ንብረቶችን እንዲያስወግዱለት ከአክሲዮን ማህበራቱ ጋር የውክልና ሽያጪ ውል የተፈራረመ ቢሆንም ከ1997 ዓ.ም እስከ 2003 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ስለሽያጩ እና ንብረቶቹ ያሉበትን ሁኔታ ክትትል ያላደረጉ መሆኑን፣

25. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ባለአደራ ቦርዱ ከተረከባቸው የተለያዩ ንብረቶች ውስጥ በአዲስ መለዋወጫ እቃዎች አስመጪና አከፋፋይ አክሲዮን ማህበር እና የቀድሞው የኢትዮጵያ ችርቻሮ ንግድ ኮርፖሬሽን የድርጅቶቹ ንብረቶች እና ባለአደራ ቦርዱ የተረከባቸው ንብረቶች በአንድ መጋዘን ውስጥ ንብረቶቹን በከፊል በቦታ በመለየት ጥበቃው በሌላ አካል ስር ሆኖ ከላይ ክፍት በሆነ ቦታ መቀመጣቸውን እንዲሁም ባለአደራ ቦርዱ ንብረቶቹን ከተረከበ ጊዜ ጀምሮ ንብረቶች ስለመኖራቸው (Existance) የማረጋገጥ ስራ ተሰርቶ የማያውቅ መሆኑን የኦዲት ግኝቱ ነበር፡፡

26. በመሆኑም በቀላሉ ሊንቀሳቀሱ እና ሊጠፉ የሚችሉ ውድ ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች የመሳሰሉትን መሰረት ባደረገ ሁኔታ እቃዎቹ ለመኖራቸው (Existance) የማረጋገጥ ስራ ሊሰራ የሚገባ መሆኑን በኦዲት ሪፖርቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

27. ባለአደራ ቦርዱም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

28. በክትትል ኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ከላይ የተጠቀሱትን ግኝቶች ለማስተካከል ባለአደራ ቦርዱ የድርጊት መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ለመ/ቤታችን ልኳል፡፡ በድርጊት መርሃ-ግብሩ ላይም ባለአደራ ቦርዱ ከህዳር 2005 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያው መሠረት ቦርዱ የሚረከባቸው ንብረቶች ለመቆጣጠር መዛግብት በመያዝ የመረከብና ወጪ የማድረግ ሥራ በተለያዩ ሠራተኞች የሚከናወን መሆኑን ገልፀዋል፡፡

29. በክትትሉም ወቅት፡-

- የንብረት ወጪ ማዘዣ የሚያዘጋጀው እና ንብረቱን የሚይዘው በተለያየ ሰው ሲሆን የምዝገባ ሥራና የንብረት ገቢና ወጭ ደረሰኞችን የሚያዘጋጀው አንድ ባለሙያ ነው፡፡
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአክሲዮን ማህበርነት ሲደራጁ ከተፈቀደላቸው ካፒታል ውጪ የሆኑ ንብረቶችን እንዲያስወግዱለት ከአክሲዮን ማህበራቱ ጋር የውክልና ሽያጭ ውል በተፈራረመው መሠረት ስለሽያጩ እና ንብረቶቹ ያሉበትን ሁኔታ ክትትሉ እየተከናወነ መሆኑን፣
- የአዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጭና አከፋፋይ አክሲዮን ማህበርና የኢትዮጵያ ችርቻሮ ንግድ ኮርፖሬሽን ድርጅት ባለአደራ ቦርድ ከተረከባቸው ንብረቶች ጋር በአንድነት በአንድ መጋዘን ውስጥ የነበሩት በአሁኑ ሠዓት የባለአደራ ቦርዱ ንብረቶች ወደ ላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ ድርጅት በመ/ቤቱ ህንፃ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚገኘው ኮንትነሮች ውስጥ እንዲቀመጥ የተደረገ መሆኑን፣ ንብረቶቹ ስለመኖራቸው (Existance) ማረጋገጥን በተመለከተ ባለአደራ ቦርዱ የሚረከባቸው ንብረቶች እስኪወገዱ ድረስ በመጋዘን ታሽጎ እንደሚቀመጡ፣ ንብረቶች ሲወገዱ ዝርዝሩን ከሀርድ ኮፒና ሶፍት ኮፒ በማየት ባላንስ የማስተካከል ሥራ እንደሚከናወን እና፣ ተሽከርካሪዎች የራሳቸው ኮድ ስላላቸው በዛ መሰረት በየጊዜው ሱፐርቪዥን በማድረግ ክትትል የሚደረግ መሆኑን፣

30. ስለጉዳዩ የባላደራ ቦርዱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በዙውን ጊዜ ውድ የሚባሉ ንብረቶች ቶሎቶሎ በሽያጭ ስለሚወገዱ ለረዥም ጊዜ በንብረት ክፍል የማይቆዩ በመሆኑ እና የሚረከቡት ንብረቶች በጣም ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ ቆጠራ ይደረግ ቢባል 10 ዓመት ሊፈጅ የሚችል በመሆኑ ቆጠራ ተደርጎ እንደማይታወቅ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

31. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የሚያስተዳድሩት ንብረት መኖሩን እና ያሉበትን ሁኔታ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ማረጋገጥ ስለሚገባ የሰጡትን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

የባለአደራ ቦርድ የንብረት አገማመት፣ የመነሻ ዋጋ አወሳሰን ፣ የጨረታ ሂደት እና የተሸጡ ንብረቶች አረካከብን በተመለከተ፣

32. አቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር የድርጅቱ ንብረት በባለሙያ ተጠንቶ የጨረታ መነሻ ዋጋ ያልተሰጠ መሆኑ እና ጨረታ ሲወጣ የጨረታ ሰነድ ዝርዝር ላይ የነዳጅ ማደያና ዲፖ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ እና ዋጋ ያልተሰጠበት መሆኑ፤ የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት ለጨረታ የቀረቡ 13 የቡና ማበጠሪያዎች፣ ጽ/ቤቶች እና መጋዘን የዋጋ ግመታ በባለሞያ አለመታየቱ፣ ጽ/ቤቶችና የቡና ማበጠሪያዎች በውስጣቸው የያዙት የማበጠሪያ ማሽን ፣ የቋሚ ንብረት ብዛት እና ዓይነት ሳይገለፅ የመነሻ ዋጋ የተሰጣቸው መሆኑ፣ የዲላ ጽ/ቤት ኤ(A) ሽያጭ ተፈፅሞ ለገዥው ርክክብ ሲደረግ ወደ ገዥው መተላለፍ ከነበረበት ንብረት ውስጥ 52 አይነት ቋሚ ንብረት ያልተላለፈ መሆኑ እንዲሁም የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት የጌምቤ ጽ/ቤትና መጋዘን በብር 555,000 ጨረታውን ካሸነፉ በኋላ ዋጋ የተሰጠው በስህተት ነው በማለት አሸናፊው ለዋስትና ባስያዘው ብር 55,000 ከመነሻ ዋጋ በ45% አንሶ የተሸጠ መሆኑ የኦዲቱ ግኝቱ ነበር፡፡

33. ባለአደራ ቦርዱ በሽያጭ የሚያስወግዳቸው ቋሚ ንብረቶች የመነሻ ዋጋ ግመታ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተሰርቶ ለጨረታ ሊቀርቡ፣ ጨረታ የወጣባቸው ንብረቶች ዓይነትና መጠን በጨረታ ሰነድ ላይ ሊጠቀስ እና ንብረቶች በጨረታ ውጤቱ መሰረት ለገዥው በትክክል መተላለፋቸው ሊረጋገጥ የሚገባ መሆኑን በኦዲት ሪፖርቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

34. ባለአደራ ቦርዱም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

35. በክትትል ኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ባለአደራ ቦርዱ ከላይ የተጠቀሱትን የኦዲት ግኝቶች ለማስተካከል የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለመ/ቤታችን የላከ ሲሆን በድርጊትት መረሃ-ግብሩም የተገለፀው የነዳጅ ማደያ ዲፖ ጨረታ ሲወጣ በጨረታ ሠነድ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተበት ምክንያት ፋብሪካው እንደ ድርጅት በጥቅል ለጨረታ በመቅረቡ ዝርዝር ላይ ባይጠቀስም የድርጅቱ ንብረቶች አካል በመሆኑ እንደሆነ እንዲሁም ድርጅቱ ለሽያጭ ከመቅረቡ ከ3 ዓመት በፊት በባንክ ባለሙያ ተገምቶ በጣም አነስተኛ ዋጋ በመሰጠቱና ጨረታ ቢወጣም

ያለውን ዕዳ ሊሸፍን የሚችል ዋጋ ላያስገኝ ይችላል ተብሎ በማሰብ እንደሆነ ተገልፀዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ማንኛውም የመንግስት ንብረት ከመወገዱ ወቅታዊው የገበያ ዋጋ መገመት በሽያጭ በመወገዱ መንግሰት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም መታወቅ ስላለበትና በሽያጭ መወገዱ ጥቅም ከሌለው ሌላ አማራጭን መፈለግ ስለሚቻል የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

የባለአደራ ቦርድ የስራ እና ሰራተኞች መመሪያን በተመለከተ፣

36. የባለአደራ ቦርዱ መቋቋሚያ አዋጅ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሰረታዊ ዓላማ በመከተል የባለአደራ ቦርድ ሰራተኞች የሚተዳደሩበት መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል ቢልም መመሪያውን ያላዘጋጀ መሆኑ ነገር ግን በሐምሌ 1/2003 ዓ.ም የሊኩዴሽን ቨርቹዋል ቲም ስራና የአሰራር መመሪያ ተዘጋጅቶ በዋና ዳይሬክተር የፀደቀ መሆኑ፣ በዚህም መመሪያ የተካተተው የሊኩዴሽን ቡድን የአበል ክፍያ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስን መሰረታዊ አላማ ያልተከተለና የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ለሊኩዴሽን ቡድን አስተባባሪ የነዳጅ ፍጆታ መጠን ያልተቀመጠ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተውቆ ነበር፡፡

37. ባለአደራ ቦርዱ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ መሰረታዊ አላማ በመከተል በመ/ቤቱ ወጥ የሆነ የሰራተኞች መመሪያ አዘጋጅቶ ሊሰራ እንደሚገባ በኦዲቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

38. ባለአደራ ቦርዱም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

39. በክትትል ኦዲት ወቅት የታየው ባለአደራ ቦርድ የድርጊት መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር የላከ ሲሆን በድርጊት መርሃ-ግብሩም የተገለፀው የፌዴራል ሲቪል ሠርቭስ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 515/99 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ለሲቪል ሠርቭስ ሠራተኞች መተዳደሪያ የሚሆኑ መመሪያዎችን ያስተላለፈላቸው በመሆኑ በዚያ መመሪያ እየሰሩ መሆኑን፣

40. ለሊኩዴሽን ቡድን አባላት ይከፈል የነበረው የትራንስፖርት አበል፣ የአበል እና የትርፍ ሠዓት ክፍያዎች ከህዳር 1/2005 ዓ.ም ጀምሮ እንዲቆሙ የተደረገ መሆኑን እና የሹፌርና የጥበቃ ሠራተኞች የትርፍ ሠዓት ክፍያዎችን በተመለከተ

ማቆም አስቸጋሪ በመሆኑ ክፍያዎቹ እንዲፈቀዱላቸው ለሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር (ለአሁኑ የሰው ሀብትና ፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር) ቀርበው ምላሽ እየተጠበቀ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

41. በክትትሉም ወቅት የታየው ለሊኩዴሽን ቡዱን አባላት ይከፈል የነበረው የትራንስፖርት አበል፣ የአደራ አበልና የትርፍ ሠዓት ክፍያ አበል የቆመ መሆኑን እና የሹፌርና የጥበቃ ሠራተኞች የትርፍ ሠዓት ክፍያን በተመለከተ ግን ሲቪል ሠርቭስ ሚኒስቴር (የአሁኑ የሰው ሀብትና ፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር) በመስፈቀድ እየተከፈላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የባለአደራ ቦርድ የክፍያና የወጪ አጠቃቀም መመሪያን በተመለከተ፣

42. የሊኩዴሽን ወጪዎችን በተመለከተ የስራ አመራር ቦርድ እንደማያየውና እንደማያፀድቀው፣ ለሊኩዴሽን ስራ ማስኬጃ እንዲወጣ በሊኩዴሽንና የድርጅቶች ንብረት አስተዳደር መምሪያ ሥራ አስኪያጅ መፈቀዱ፣ በተፈቀደው መሰረት ለጥቃቅን ወጪ በየወሩ እንዳለቀ የሚተካ ለቡና ግዥና ሻያጭ ድርጅት ብር 3,000 እና ለአቃቂ ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ማህበር ብር 2,500 እየተከፈለ እና ከ2001-2003 በጀት ዓመት ለጥቃቅን ወጪዎች ተብሎ በድምሩ ብር 172,037.56 ወጪ መደረጉ፣ ክፍያውም በዋናነት ለመስተንግዶ፣ ለነዳጅና ለመሳሰሉት የሚውል መሆኑ፣ ባለአደራ ቦርዱ ከአቃቂ ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ማህበር ከተረከበው ነዳጅ እንዲጠቀም በስራ አመራር ቦርድ ሳይፈቀድ ተጠቅሞ መገኘቱ፣ በርክክብ ወቅት 7,410 ሊትር ቤንዚን እና 5,725 ሊትር ናፍጣ በህዳር 2001 ዓ.ም የተረከቡ ቢሆንም በካርድ ባላንስ መሰረት «oct 17/2011» 192 (2.59%) ሊትር ቤንዚን እና «May /2011» 1257 (22%) ሊትር ናፍጣ የቀረ እና 7,218 ሊትር ቤንዚን ና 4,468 ሊትር ናፍጣ የተጠቀሙበት መሆኑን፣

43. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው በባለአደራ ቦርዱ መቋቋሚያ አዋጅ በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 3 የስራ አመራር ቦርዱ የባለአደራ ቦርዱን ስራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤ የሚፈርሱ የልማት ድርጅቶች ሂሳብ የማጣራት ሂደት ሕጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ መፈፀሙን ያረጋግጣል ይላል በዚህ መሰረት የሊኩዴሽን ወጪዎቹም የቦርዱ ሃላፊነት በመሆናቸው ወጪዎችን አለማየትና አለማፅደቅ ኃላፊነትን ካለመወጣቱም ባሻገር ወጪዎች በትክክለኛው መንገድ መውጣታቸውን

የማያረጋግጥ መሆኑ እንዲሁም ባለአደራ ቦርዱ በአደራነት የተረከበውን ንዳጅ የበላይ ኃላፊዎች ሳይፈቅዱ መጠቀም የተቀዳው ንዳጅ በአግባቡ ስራ ላይ እየዋለ መሆኑን ለመቆጣጠር የማያስችልና ለብክነት የሚያጋልጥ መሆኑን በኦዲት ግኝቶ ታይቶ ነበር፡፡

44. የስራ አመራር ቦርዱ የፈረሱ የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ለማጣራት የሚወጡ ወጪዎች ህጋዊ ስርአቱን ተከትሎ መፈጸሙን ሊያረጋግጥ የሚገባ መሆኑን የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

45. ባለአደራ ቦርዱም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

46. ባላአደራ ቦርዱም የተጠቀሱትን ግኝቶች ለማስተካከል በቀን 9/2005 ዓ.ም የድርጊት መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ለመ/ቤታችን የላከ ሲሆን በድርግት መርሃ-ግብሩም የተጠቀሰው የፈረሱ የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ለማጣራት ለልኩዴሽን ቡድን ሥራ ምን ያህል ወጪ እንደሆነ /ለደመወዝ፣ ለነዳጅ፣ ለመስተንግዶና ለሌሎች ወጪዎች/ በወጪ አርዕስቶች መሠረት በዝርዝር ተዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርድ እንዲቀርብ ተብሎ ለሊኩዴሽን ቡድን አስተባባሪዎች ኃላፊነት የተሰጣቸው ቢሆንም በክትትል ኦዲት ወቅት ግን በሁሉም ሊኩዴሽን ቡድን መሪዎች ለሥራ አመራር ቦርዱ የቀረበ የወጪ ሪፖርትና በሥራ መራር ቦርዱ የተወሰደ እርምጃ ስለመኖሩ የሚያስረዳ መረጃ በክትትል ኦዲቱ ወቅት አልቀረበም፡፡

ባለአደራ ቦርዱ በተለያየ መንገድ ይዞታቸው ከተለወጡ እና በኪሳራ ምክንያት ከፈረሱ የልማት ድርጅቶች የተረከባቸውን የማይተላለፉ ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ መሰብሰባቸውን፣ ተከፋይ ሂሳቦች በአግባቡ ተጣርተው የሚከፈል መሆኑን የሚያረጋግጥ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

47. ባለአደራ ቦርዱ ውስጥ ይዞታቸው የተቀየሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሂሳብ ስራ ተረክቦ ለማከናወን በየበጀት ዓመቱ እቅድ የሚያዘጋጅ ቢሆንም ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት ክንውኑ ዝቅተኛ መሆኑን፣ ባለደራ ቦርዱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች እንዳይታወቅና የተጠቃለለ የሂሳብ

መግለጫ (Consolidated Financial Report) እንዳይዘጋጅ ያደረገ መሆኑ በኦዲቱ ግኝቱ ታውቆ ነበር፡፡

48. የፈረሱ የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ ማጣራት ስራዎች ከመጀመራቸው በፊት እቅድ እና የድርጊት መርሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ሊተገበር የሚገባ መሆኑን በኦዲቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

49. ባለአደራ ቦርዱም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

50. በክትትል ኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ባለአደራ ቦርዱ የተጠቀሱትን ግኝቶች ለማስተካከል የድርጊት መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ለመ/ቤታችን የላከ ሲሆን በመርሃ-ግብሩም ላይ የተገለፀው ከ2001-2003 በጀት ዓመት ድረስ የሂሳብ ማስመርመር ሥራ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በታህሳስ ወር 2005 ዓ.ም ጀምሮ መርሃ-ግብር ተዘጋጅቶ የሚቀርብ መሆኑን የገለፁልን ቢሆንም፣

51. በክትትል ኦዲቱም ወቅት የታየው እንተገብረዋለን ብለው በላኩት የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት የሂሳብ መዝጋትና የተጠቃለለ መግለጫ ለማዘጋጀት የድርጊት መርሃ ግብር ያልተዘጋጀ እና የሂሳብ መግለጫው ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡ ስለጉዳዩ የባለአደራ ቦርዱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የተዘጋጀ የድርጊት መረሃ ግብር ባይኖርም በአክፓክ ሶፍት ዌር እንዲሰራ እቅድ የተያዘ ሥራው ከተጀመረው በመ/ቤታችን በአዋጅ ከተቋቋመ ከ11 ዓመት በኃላ በመሆኑና በበአክፓኩ የሠለጠኑ ባለሙያዎች መ/ቤቱን በመልቀቃቸውና ድርጅቱ ከነበረበት ሥፍራ ለ3 ጊዜ ያህል የቢሮ ለውጥ በማድረጉ የሲስተም መቆራረጥና እንደገና መዘርጋት ጊዜ በመውሰዱ እንዲሁም በአዲስ መልክ የአክፓኩ ሥራ ተቋርጦ በሌላ ሲስተም እንዲሰራ በ2008 ዓ.ም ለሌላ አማካሪ ድርጅት የተሠጠ ቢሆንም ሥራው እስከ አሁን ተጠናቀው አፋጣኝ እርምጃ ለመውሰድ ያልተቻለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የፈረሱ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ለማጣራት የተዘጋጀ እቅድ እና የእቅድ ክንውኑን በተመለከተ፣

52. በናሙና ከታዩት በባለአደራ ቦርድ ሂሳብ ማጣራት ስራ ከተከናወነባቸው ድርጅቶች ውስጥ የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት እና የአቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር

ስራውን ለመስራት በቅድሚያ የተዘጋጀ እቅድ እና የድርጊት መርሃ ግብር አለመኖሩ እና የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት ከፈረሰ ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ.ም ለ10 ዓመታት በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን እንዲሁም ከ 2001 እስከ ህዳር 2004 ዓ.ም ለአራት ዓመታት የሂሳብ ማጣራት ስራ በባለአደራ ቦርድ እየተሰራ ቢሆንም ስራው ያልተጠናቀቀ መሆኑ በኦዲት ግኝቱ ታውቆ ነበር፡፡

53. ባለአደራ ቦርዱም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

54. በክትትል ኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ባለአደራ ቦርድ ግኝቶችን ለማስተካከል የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለመ/ቤታችን የላከ ሲሆን በመርሃ-ግብሩም የተገለፀው በተለያየ ምክንያት የፈረሱ የልማት ድርጅቶች ሂሳብ ለማጣራት የድርግት መረሃ-ግብር ዕቅድ የሚያዘጋጁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

55. በክትትሉ ኦዲቱም ወቅት የታየው ሂሳቡን ለማጣራት የድርጊት መርሃ-ግብር ስለመዘጋጀቱ የሚያስረዳ መረጃ ክትትሉ እስከ ተጠናቀቀበት እለት አልቀረበም፡፡ነገር ግን የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት እና የአቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበርን ጨምሮ የ263 የልማት ድርጅቶች የ20 ዓመት ሂሳብ ተጠቃሎ ተሠርቶ ለኦዲት ሥራ የተዘጋጀ መሆኑን በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ አስረዷቷል፡፡

ክፍል ሦስት

መደምደሚያ

56. በመንግስት የልማት ድርጅቶች በኣለአደራ ቦርድ የሚከናወኑ ሥራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከናውኖ በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- ባለአደራ ቦርዱ በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ግኝቶችንና የተሰጠ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማስተካከልና ተግባራዊ ለማድረግ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላከ መሆኑን፣
- ባለአደራ ቦርዱ ሁሉም ውሳኔዎች እንዲያጸድቁ ለሥራ አመራሩ ቦርዱ ይላክ የነበረውን አሠራር በመቆም በመንግሰት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት እየተሠራ በመሆኑ በሥራ ላይ ይደረስ የነበረውን መዘግየት የቀነሰ መሆኑን፣
- ባለአደራ ቦርድ የመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ፡-
    - በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት ከባለአደራ ቦርድ የሥራ በህሪ አንፃር የማያሰሩትን አንቀፆች በመለየት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር (አሁን የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር) ጥያቄ አቅርበው በማስፈቀድ ተግበራዊ ያደረገ መሆኑን፣
    - ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አቅርበው ያልተፈቀደላቸው አንቀፆች በመመሪያ ቁጥር 9/20003 መሠረት እየሠሩ መሆኑን እና
    - ባለአደራ ቦርድ የሚረከባቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ንብረት የዋጋ ክለሳ ሳይደረግ ይከራይ የነበረው አሠራር ተሻሽሎ ያለጨረታ የሚከራይ ምንም ዓይነት ንብረት የሌለ መሆኑን፣
- ባለአደራ ቦርዱ ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ (አሁን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር) የሚረከበውን ንብረቶች

በመጠን፣ በዓይነትና በዋጋ ለይተው በዝርዝር የመረከቡ ሥራ ከህዳር 2005 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን፣

- ባለአደራ ቦርዱ ከህዳር 2005 ዓ.ም ጀምሮ የንብረት ወጪ ማዘዣ የሚያዘገጀው እና ንብረቱን የሚይዘው በተለያየ ሰው ሲሆን የምዝገባ ሥራና የንብረት ገቢና ወጭ ደረሰኞችን የሚያዘጋጀው አንድ ባለሙያ መሆኑን፣
- ባለአደራ ቦርድ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአክሲዮን ማህበርነት ሲደራጁ ከተፈቀደላቸው ካፒታል ውጪ የሆኑ ንብረቶችን እንዲያስወግዱለት ከአክሲዮን ማህበራቱ ጋር የውክልና ሽያጪ ውል በተፈራረሙ መሠረት ስለሽያጩ እና ንብረቶቹ ያሉበትን ሁኔታ ክትትል እየተደረገ መሆኑን፣
- የአዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጭና አከፋፋይ አክሲዮን ማህበርና የኢትዮጵያ ችርቻሮ ንግድ ኮርፖሬሽን ድርጅት ባለአደራ ቦርድ ከተረከባቸው ንብረቶች ጋር በአንድነት በአንድ መጋዝን ውስጥ የነበሩት ንብረቶች ወደ ላይኛው አዋሽ አግሮ እንዱስቱሪ ድርጅት በመጓጓዝ በመ/ቤቱ ህንፃ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚገኘው ኮንትነሮች ውስጥ እንድቀመጥ የተደረገ መሆኑን፡
- ባለአደራ ቦርዱ የፌዴራል ሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር አዋጅን መነሻ በማድረግ የባለአደራ ቦርድ ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን መመሪያ ማዘጋጀትን በተመለከተ፡
  - ባለአደራ ቦርዱ የፌዴራል ሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 515/99 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ለሲቪል ሠርቪስ ሠራተኞች መተዳደሪያ የሚሆኑ መመሪያዎችን ያስተላለፈላቸው በመሆኑ በዚያ መመሪያ እየሰሩ መሆኑን፣
  - ለሊኩዴሽን ቡድን አባላት ይከፈል የነበረው የትራንስፖርት አበል፣ የአቧራ አበል እና የትርፍ ሠዓት ክፍያዎች ከህዳር 1/2005 ዓ.ም ጀምሮ እንዲቆሙ የተደረገ መሆኑን፣
  - የሹፌርና የጥበቃ ሠራተኞች የትርፍ ሠዓት ክፍያዎችን በተመለከተ ማቆም አስቸጋሪ በመሆኑ ክፍያዎቹ እንዲፈቀዱላቸው ለስቪል ሠርቭስ ሚኒስቴር አቅርበው በማስፈቀድ ክፍያ እየተፈፀመ መሆኑን፣
- ሂሳቡን ለማጣራት የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት እና የአቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበርን ጨምሮ የ263 የልማት ድርጅቶች የ20 ዓመት ሂሳብ ተጠቃሎ የተሰራ መሆኑ፣

3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸውና መሻሻል ያልታየባቸው

57. ባለአደራ ቦርዱ ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግሰት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ (አሁን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር) ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያሰችል የመግባቢያ ሠነድ ጥናትም ሆነ የተዘጋጀ የመግባቢያ ሠነድ የሌለ መሆኑን፣

58. ባለአደራ ቦርዱ ተረክቦ በመጋዘን የሚያስቀምጣቸው ንብረቶች ስለመኖራቸው (Existance) ለማወቅ የንብረት ቆጠራ ቢያንስ በአመት አንዴ ቆጠራ በማድረግ የማያረገግጥ መሆኑ፣

59. የፈረሱ የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ለማጣራት ለልኩዴሽን ቡድን ሥራ ምን ያህል ወጪ እንደሆነ /ለደመውዝ፣ ለነዳጅ፣ ለመስተንግዶና ለሌሎች ወጪዎች/በወጪ አርዕስቶች መሠረት በዝርዝር ተዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርድ እንድቀርብ የሚደረግ መሆኑን በላኩልን የድርጊት መርሃ-ግብረ የገለፁልን ቢሆንም ለሥራ አመራር ቦርዱ የቀረቡት የወጭ ሪፖርትና በሥራ መራር ቦርዱ የተወሰደ እርምጃ የሌለ መሆኑን፣

60. ከ2001-2003 በጀት ዓመት ድረስ የሂሳብ ማስመርመር ሥራ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በታህሳስ ወር 2005 ዓ.ም ጀምሮ መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ የቀርባል ተብሎ ለመ/ቤታችን በተላከው የድርጊት መርሃ-ግብር ላይ ይዘጋጃል ተብሎ በተገለጸው መሠረት ሂሳቡን ለማስመርመር የተዘጋጀ የድርጊት መርሃ-ግብር የሌለ መሆኑን፣

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

61. ከላይ በክፍል ሁለት ላይ የተጠቀሱ ነባራዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የተደረሰባቸው መደምደሚያዎች በክፍል ሦስት ላይ ተጠቅሰዋል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች ላይ በአብዛኞቹ የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክሮ መቀጠል አለባቸው፡፡

62. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ያልተስተካከሉና የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸው እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አሁንም የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸውና አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም የድርጊት መርሃ ግብርም ለመ/ቤታችን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መላክ አለበት፡፡

በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአለአደራ ቦርድ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡